# ጋዜጦቻችን

*የዚህ አምድ ዋና አላማ በየሳምንቱ በሀገራችን ታትመው የሚወጡ በተለይም የዜናና የመረጃ ጋዜጦችን እንዲሁም መጣጥፎችን የሚዳስስ ይሆናል፡፡*

*www.EthiopiaFirst.com በጋዜጣዎቹ ወይንም በመጣጥፎቹ ላይ የወጡትን ፅሁፎች እንደወረዱ ከማቅረብ በስተቀር ማስተካከልም ሆነ መጨመር ብሎም መቀነስ አታደርግም፡፡*

*ጋዜጣዎቹና መጣጥፎች በሚይዙት የዜናና የመረጃ ጥልቀት የሚመረጡ ሲሆን በተቻለ መጠን የሚወጡትን ሳምንታዊ የመረጃ ጋዜጦች ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡*

*****************************************************************************

## ለመስከረም 22 የተቃውሞ ሰልፍ ሊጠራ ነው

(ፍትህ ቅፅ 04 ቁጥር 150 ነሐሴ 20 2003 ገፅ 14)

የመላው ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /መኢዴፓ/ እና የኢትዮጵያ አንድነት ዴሞክራቲክ ፓርቲ ሰላማዊ ሰልፍ ለመጥራት ለከንቲባው ጽ/ቤት «ለስብሰባ እና ሰላማዊ ሰልፍ ፍቃድ ክፍል» ማስታወቃቸውን ፓርቲዎቹ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

መስከረም 22/2004/ በመስቀል አደባባይ ሊካሄድ የታሰበው ሰላማዊ ሰልፍ ከጠዋቱ 3-8 ሰዓት እንደሚቆይ ገልፀዋል፡፡ በህግ እንደተቀመጠው አንድ ሰላማዊ ሰልፍ ሲጠራ ከ48 ሰዓት ቀድሞ ማሳወቅ ግዴታ ቢሆንም ከሰልፉ ጥሪ ከ1 ወር በፊት አስቀድመው ማስታወቃቸውን ገልፀዋል፡፡

## የጋዜጠኛ ውብሸት መደብደብ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ለጠ/ሚ መለስ ጥያቄ ቀረበ

(አውራምባ ታይምስ 4ኛ ዓመት ቁጥር 182 ነሐሴ 21 ገፅ1)

በሽብር ተግባር ተጠርጥሮ በእስር ላይ የሚገኘው የአውራምባ ታይምስ ም/ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ በመርማሪ ፖሊሶች ድብደባ እንደተፈፀመበት ለፍ/ቤት ማመልከቱን ተከትሎ «ሪፖርተርስ ዊዝአውት ቦርደርስ» የተሰኘ ዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች መብቶች ተሟጋች ቡድን ጉዳዩ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ለጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፃፈው ደብዳቤ መጠየቁ ተዘገበ፡፡

ከውብሸት በተጨማሪ በእስር ላይ የምትገኘው የፍትሕ ጋዜጣ አምደኛ ወ/ሪት ርዕዮት ዓለሙ በመልካም ጤንነት ላይ አለመገኘቷን ጋዜጠኞቹ ያሉበት ሁኔታ በጣም አስደንጋጭና የምርመራ ጊዜያቸውም መራዘሙ አሳሳቢ እንደሆነበትና ጋዜጠኞቹም በአፋጣኝ እንዲፈቱ ቡድኑ ለጠ/ሚኒስትሩ በፃፈው ደብዳቤ መጠየቁን ዘገባውን ያሰራጨው ድረ-ገፅ (all African.com) አስነብቧል፡፡

# ‹‹ለሊቢያ ድጋፍ ለማበርከት ጊዜው አልረፈደም›› አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ

(አውራምባ ታይምስ 4ኛ ዓመት ቁጥር 182 ነሐሴ 21 ገፅ19)

በሊቢያ ከስድስት ወራት በፊት የተጀመረው ሕዝባዊ ተቃውሞ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ በመቀጠል ተቃዋሚዎች የሀገሪቱን ዋና መዲና ትሪፖሊን መቆጣጠራቸውን ተከትሎ ኢትዮጵያና ናይጄሪያ ለሀገሪቱ ብሔራዊ ሽግግር ካውንስል ዕውቅና ሰጡ፡፡

ረቡዕ ማምሻውን የሁለቱ ሀገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በአዲስ አበባ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም የሊቢያን ሕዝብ ደህንነት ለማስጠበቅ ሲባል ብሔራዊ የሽግግር ካውንስሉን እንደ ሕጋዊ የሊቢያ አስተዳዳሪ መቀበላቸውን አሳውቀዋል፡፡

«ሰላም ወዳድ ሀገራት በሙሉ በተለይም የአፍሪካ ሕብረት የሽግግር ካውንስሉን በመደገፍና ዕውቅና በመስጠት ለሊቢያ ሰላምና መረጋጋት አስተዋፅኦ ማበርከት አለባቸው» ላሉት ሚኒስትሮች አውራምባ ታይምስ «ይኼ ድጋፍ የዘገየ አይመስላችሁም» የሚል ጥያቄ ቀርቦ ነበር፡፡ የኢፌዴሪ ምክትል ጠ/ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ ድጋፉ የዘገየ አለመሆኑንና ይልቁንም ድጋፍ የማበርከቻው ሰዓት አሁን መሆኑን በመግለፅ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡